# የዳግመ ግምገማ ስብሰባ፡ የቤተሰብ/አሳዳጊ አጠቃላይ እይታ

የተማሪ ስም፡-  ቀን፡-

**የዳግመ ግምገማ ስብሰባ ምንድነው?**

በየሶስት አመቱ (ወይም አስፈላጊ ከሆነ ፈጥኖ)፣ ልጅዎ አሁንም ለልዩ ትምህርት እና/ወይም ተዛማጅ አገልግሎቶች ብቁ መሆናቸውን ለማየት ትምህርት ቤቱ እንደገና ግምገማ እንዲያካሄድ ይፈለጋል። ይህ ከመሆኑ በፊት፣ ልጅዎ አሁንም ለአገልግሎቶች ብቁ መሆኑን ለማወቅ እርስዎ እና የትምህርት ቤት ቡድንዎ አዳዲስ ግምገማዎች (እንደ ፈተናዎች ወይም ምልከታዎች) አስፈላጊ ከሆነ ሲወስኑ የዳግመ ግምገማ እቅድ ማውጣት ስብሰባ ያደርጋል።

**በአብዛኛው ጊዜ በዳግመ ግምገማ ስብሰባ ላይ የሚሳተፈው ማነው?**

- እርስዎ *(ወላጅ ወይም አሳዳጊ)*
- የልጅዎ አስተማሪዎች *(አጠቃላይ እና ልዩ ትምህርት)*
- ርእሰ መምህር፣ ረዳት ርእሰ መምህር ወይንም ተወካይ የሰራተኛ አባል
- ልጅዎ ተዛማጅ አገልግሎት የሚያገኙ ከሆነ የዛማጅ አገልግሎት ሰጪዎች *(እንደ ንግግር ቴራፒስት፣ የኦኪፔሽናል ቴራፒስት (OT)፣ የአካል ቴራፒስት(PT) ወዘተ)*
- የተማሪ ድጋፍ አስተባባሪ *(SSC)*
- ልጅዎ *(ተገቢ ሲሆን)*
- የትምህርት ቤት የስነ ልቦና ባለሙያ
- የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሰራተኛ
- በእርስዎ ወይም በትምህርት ቤቱ የተጋበዘ ሌላ ሰው

**ስለ ምን እንወያያለን?**

በስብሰባው ላይ ቡድኑ የሚከተሉትን ያደርጋል፡-
- ስለልጅዎ የተጠናቀቁትን ሁሉንም ወቅታዊ መረጃዎች እና ግምገማዎች ይገምግማሉ። ልጅዎን የገመገሙ ሰራተኞች ግኝቶቻቸውን ይገመግማሉ እና ያጠቃልላሉ።
- ቡድኑ እርስዎ የሚያጋሯቸውን መረጃዎች ጨምሮ ሁሉንም ግብአቶች ግምት ውስጥ ያስገባል።
- የብቁነት ቅጾችን በመጠቀም፣ ቡድኑ አሁንም ልጅዎ በትምህርታቸው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ እና ልዩ ትምህርት የሚጠይቁትን የአንድ ወይም ከዚያ በላይ የትምህርት አካል ጉዳተኝነትን መመዘኛዎችን ማሟላታቸውን ወይም አለማሟላታቸው ይመረምራል።

**የሚወሰነው ምንድነው?**

ቡድኑ ልጅዎ ለልዩ ትምህርት አገልግሎት ብቁ ሆኖ መቀጠል መቻላቸውን ወይም አለመቻላቸውን እና የትምህርት አካል ጉዳተኝነት/አካል ጉዳተኝነቶችን ምንነት ይለያል።

## በዳግመ ግምገማ ስብሰባው እንደ ወላጅ/አሳዳጊ ያለኝ ሚና ምንድን ነው?

- በስብሰባው ወቅት ውይይቱ ላይ ንቁ ተሳትፎ ያድርጉ። ማስታወሻ፡ ለመሳተፍ የቋንቋ ትርጉም እና/ወይም የADA መስተንግዶ ከፈለጉ ትምህርት ቤቱን ያሳውቁ።
- ሃሳቦችዎን፣ አመለካከቶችዎን እና የሚኖርዎትን ማንኛውንም ስጋት ለማካፈል አያመንቱ።
- እንደየ አስፈላጊነቱ ጥያቄዎችን እና ማብራሪያ ይጠይቁ።

ማስታወሻ፡ ትምህርት ቤቱ የልጅዎን የብቁነት ምደባ እንዲቀይር እንዲሁም ልጅዎን ከልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ለማስወጣት የእርስዎ ፈቃድ ያስፈልጋል።

## ለዳግመ ግምገማ ስብሰባ መዘጋጀት

የበለጠ ዝግጁነት እና በራስ የመተማመን ስሜት እንዲሰማዎት የሚከተሉት ነገሮችን ማድረግ ይችላሉ፦

- ☑ የወላጅ ትረካ ለመጻፍ ያስቡበት እና ቡድኑ እንዲያስብበት አስቀድመው ያስገቡት። የወላጅ የመረጃ ማእከል *(PRC)* ከእርስዎ ጋር ሊያጋሯቸው የሚችሉ የወላጅ ትረካዎች ናሙና አልዋቸው።
- ☑ ማጋራት የሚፈልጓቸውን ማናቸውንም የግል ሪፖርቶች (ግምገማዎች፣ የህክምና ሪፖርቶች) ያሰባስቡ እና ከስብሰባው በፊት ያቅርቡ።
- ☑ ቡዱኑ ግምት ውስጥ ያስገባቸውን የአካል ጉዳት ምድብ ለመለየት የብቁነት ቅጾችን ይገምግሙ።

- ☑ የብቁነት ፓኬጅ ትምህርት ቤቱ ካከናወናቸው የምዘናዎች ሪፖርቶች ጋር ከብቁነት ስብሰባው ቢያንስ ሁለት ቀናት በፊት ይገኛል። ከስብሰባው ቢያንስ ከሁለት ሳምንታት በፊት ፓኬጁን ከትምህርት ቤትዎ ልዩ ትምህርት አስተዳደር ረዳት ለመቀበል ዕቅዶችን ያረጋግጡ።
- ☑ የግምገማ ፓኬጁን ከሁሉም የግምገማ ክፍሎች ጋር በጥንቃቄ ለመገምገም ጊዜ ይስጡት።
- ☑ በስብሰባው ወቅት መጠየቅ የሚፈልጉትን ጥያቄዎች ከታች "የመነጋገሪያ ነጥቦች" የሚለው ክፍል ላይ ይጻፉት።
- ☑ በስብሰባው ወቅት መጠየቅ የሚፈልጉትን ጥያቄዎች ከታች "ጥያቄዎች" የሚለው ክፍል ላይ ይጻፉት።
- ☑ ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም ለስብሰባዎ ለመዘጋጀት ድጋፍ ከፈለጉ የወላጅ መረጃ ማእከልን (PRC) ያግኙ።
- ☑ አንድን ሰው (እንደ ጓደኛ፣ ጠበቃ ወይም የቤተሰብ አባል) ከእርስዎ ጋር ወደ ስብሰባው ለማምጣት ካሰቡ  ቦታ እና ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት እንዲችል ትምህርት ቤትዎ አስቀድመው ያሳውቁ።

| ሊታሰብባቸው የሚገባ ጥያቄዎች | የመነጋገሪያ ነጥቦች/ተጨማሪ ጥያቄዎች |
|---|---|
| • የዛሬ ውሳኔዎቻችን ወይም ከአዳዲስ ምዘናዎች ያገኘነው መረጃ የልጄን የIEP ድጋፍ/አገልግሎቶች ላይ ተጽእኖ ያሳድራል?<br>• በዚህ ስብሰባ ላይ ስለተደረገው የውሳኔ ሰነድ መቼ ነው የምቀበለው?<br>• በዛሬው ስብሰባ ውጤት ካልተስማማሁ ምን ማድረግ አለብኝ? | |

LEARN MORE

እርስዎ ለመርዳት PRC እዚህ ይገኛል። 703.228.7239 ላይ ይደውልሉን ወይም prc@apsva.us ኢሜል ይላኩልን።

PEATC:- ጠቃሚ የወላጅ መብቶች

PEATC:- ምዘናዎችን መረዳት

VDOE: የዳግመ ግምገማ ቪድዮ

PEATC: ዳግመ ግምገማ

PEATC: ቤል ከርቭ እና ደረጃውን የጠበቀ ፈተና